# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ለወጣቱ መልእክት

በቅድሚያ እንኳን ለሶስተኛው ጉባዔችሁና ለሁለተኛው አመት የምሥረታ በዓል አደረሳችሁ እላለሁ;

የዛሬዋ ቀን ከእናንት አንደበት ብዙ ለመስማት የምንጓጓንባት እለት ነች። አላማችሁን፤ አቋማችሁን፤ ያከናወናችሁትና ያቀዳችሁትን ለመረዳት ለጥያቄዎቻቸው መልስ ለማግኘት ብዙ ሰዎች ሲጠብቋት የነበረች ቀን ነች። ጊዜውን መሻማት ስለማልፈልግ የማስተላልፍው በጣም አጭር መልእክት ነው።

በማንኛውም ጊዜ ቦታና ሁኔታ ወጣት ትውልድ የአንድ ህብረተሰብ የጀርባ አጥንት ነው፤፡ የወጣቱ እድልና ተስፋ ከሀገሪቱ የወደፊት እድልና ተስፋ ጋር የተያያዘ ነው፤ ስለ ሆነም ወጣቱ ትውልድ በሀገሪቱ ሕይወት ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ሀገሪቱ ሀብቷንም ሆን ድህነቷን ፤ ስላሟንም ሆነ ጦርነትን፤ መረጋጋትንም ሆነ ሽብርን የምታወርሰው ለወጣቱ ትውልድ ሲሆን የወደፊቱ የሀገሪቷ ሁኔታ የሚወሰነው አቅጣጪያ የሚይዘው ደግሞ በወጣት ትውልድ ጥረትና ሥራ ነው። ወጣቱ ትውልድ ለራሱ ብቻ የሚያስብ፤ በተለያየ ልምድ የተበከለ፤ ለሀገሩና ለወገኑ እድገት ራእይ የሌለው ከሆነ አገሪቷ ከድህነት ከስቃይና ከጦርነት ወዘተ... የምትላቀቅበት እድል የመነመነ ሲሆን ባንጻሩ ወጣቱ ለሀገርና ለወገኑ ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ፣ ብሩህ ተስፋና ጥልቅ ራእይ ያለው፣ ታታሪና ጠንካራ ከሆነ ደግሞ አገሪቷ ካላችበት ድህነት ችግርና መከራ ባፋጣኝ ተላቃ ምቾትና ሰላምንና ብልጽግናና መብትን ለሕዝቦቿ ልታዳርስ ትችላለች። ስለዚህም ነው የዛሬ 20 30 40 50 አመት ወደፊት አመትረን ስናይ የአንድ አገር የወደፊት ሁኔታና የወጣቱ ትውልድ እድል የተያያዘ የሚሆነው። በመሆኑም ወጣቱ ትውልድ የአገሪቷን የወደፊት ሁኔታና መልክ በመቅርጽ በኩል ከፍተኛ ሃላፊነትና ሚና አለው።

በአለም ላይ በየአገሩ አገራቸውን ከባእድ አገዛዝ ለማላቀቅ ፤ አምባገነነና ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞችን ለመፋለም ፤ የሕዝባቸውን መብት ለማስከበር፤ አገራቸውን ከድህነትና ከኋላ ቀርነት አላቀው ልማትና እድገት ለማስገኘት ወጣቶች የሚጫወቱትን ሚና ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። ይህንነ እውነታ ለመረዳት የአለምን የታሪክ ማህደር ማገላበጥ አይጠይቀንም። ባለፈው አመት በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ በሚገኙ አሬብ አገሮች የተካሄዱት የሥርአት ለውጥ እንቅስቃሴዎች በመረመር ብቻ የወጣቶች ሚና ምን ያህል መሆኑን መረዳት እንችላለን።

በሀገራችን የቅርብም ሆነ የሩቅ ታሪክ የሀገራችንን ጠላቶች በመፋለም የሀገራችንን ህልውና በማስጠበቅ ለሀገራችን እድገት ለሕዝባችን አንድነት ወጣቶች የተጫወቱት ወሳኝ ሚና ዛሬ የሚካድ አይደለም። የሩቁን ትተን የቅርቡን እንኳ ብንወስድ በአድዋ፤ በማይጨውና በአምስቱ የጣሊያን ቅኝ ግዛት ዘመን ቅኝ የውጭ ጠላቶችን የተፋለሙት ወጣቶች ናቸው። ቀደም ባለው ዘመንም ለሀገራችን ዘማናዊ ትምህርትን፡ ዘመናዊ ህክምናና ዘመናዊ አስተዳደርን ወዘተ... በማስተዋወቅም ሆነ ተግባራዊ በማድረግ በኩል ግምባር ቀደም ሚና የነበራቸው በዚያን ወቅት የትምህርት እድል ያገኙት ወጣቶች ናቸው። በሀገራችን የንግድና የልማት ተግባር ላይ በመሳተፍ ሀገራችንን ከኋላ ቀርነት ለማላቀቅ ጥረት ያደረጉት ወጣቶች ናቸው። በዚህ በኩል ብዙ ብዙ ማለት ይቻላል።

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

እኛም ወጣት ሆነን ባለፍንበት ወቅት የአጼው አገዛዝ አክትሞ የተሻለ የፖለቲካ ሥርዓት እንዲመጣ በመታገል ከፍተኛ አስተዋጾ ያደርገው የተማሪው እንቅስቃሴ የወጣት እንቅስቃሴ ነበር። ኢሕአፓን የመሠረተው ወጣት ትውልድ ነበር። ከተመሠረተም በሃላ እንቅስቃሤ በማድረግ የታገለው በአብዛኛው ከ30 አመት በታች የነበረ ወጣት ትውልድ ነው። አምባገነነትን በመፋለም የቀይ ሽብርና የነጻ እርምጃ ጽዋ የቀመሰው፤ ከፍተኛ መስዋእትነትን የከፈለው ዘጠና ከመቶ የሚሆነው ወጣት ትውልድ ነበር። የወያኔን አምባገነን አገዛዝን በተለያዩ ጊዜያት የግንቦት 97 ምርጫ ጨምሮ በግምባር ቀደምትነት የተፋለሙት ወጣቶች ናቸው።

ከአለም አቀፉና ከአገራችን ታሪክ ለፍትሕ፤ ለዴሞክራሲና ለእኩልነት የሚደርገውን ትግል አስመልክቶ ወጣቱን የሚያመሳስል ልዩ ባህርይ አለ። ወጣት ግፍና በደልን ይቃወማል፤ ወጣት የፍትሕ እጦትን ይቃወማል፣ወጣት ኋላ ቀርነትንና ድህነትን ይቃወማል፤ ወጣት አምባገንንነትን ይፋለማል፣ ወጣት ለሀገሩ ራሱን አሳልፎ ይሰጣል።

በጸረ ኢትዮጵያው ከፋፋዩና አምባገነኑ ወያኔ እየተሰቃየች የምትገኘው አገራችን የታጋይ ያለህ፡ የጀግና ያለህ በማለት ድምጿን ከፍ አድርጋ በምታጣራበት ወቅት፤ ሕዝባችንን ከአስከፊው አምባገነን አገዛዝ የሚያላቅቅ በሺ በሚሊዮን የሚቆጠር አገር ወዳድ፤ ወጣት በሚፈለግበት ሰዓት፤ ከራስ ጥቅምና ምኞት ይልቅ ለወገን ችግርና ብሶት የሚያስብ ዜጋ በጽኑ በሚፈልግበት አፍላ ወቅት የኢህአፓን ፈለግ በመከተል ኢህአፓ ወክንድ በሚል ስያሜ በመደራጀት ለአገራችሁ ለወገናችሁ አርነት ቁርጥ ትግል ለማድረግ ቆርጣችሁ በመነሳታችሁ ልትኮሩበት ይገባል። ለሀገርና ለወገን ደህነነት የራስን ጥቅም፤ የራስን ኑሮ የራስን ህይወት ከመስጠት በላይ የሚያኮራ ተግባር ሊኖር አይችልም። ስለሆነም ድርጅታችሁን በሀገር ውስጥም በውጭም በማስፋት የትግሉ አጋርና ተሳታፊ የሚሆኑ በሺ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣቶችን አፍሩ ነው መልክታችን።

እኛ ትግል ስንጀምር ተመክሮ አልነበረንም። በሀገሪቷም የፖለቲካ ድርጅት ስላልነበረ ከዚህ ድርጅት ተሞክሮም ሆነ ትምህርት ልንቀስም አልቻልንም። ሁሉንም በአዲስ መንገድ በራሳችን ጥረት ለመታገል ነው የሞከርነው። ስለሆነም እየሠራን፤ እየተሳሳትን ከስህተታችን እየተማርን ትግሉን አስቀጥለናል። እናንት ቢያንስ በአንድ ጉዳይ እድለኞች ናችሁ። ካለፈው ትውልድ ስህተትም ሆነ በጎ ተግባር ብዙ መማር ትችላላችሁ።

አንዳንድ ነጥቦችን አንስቼ ይችን አጭር መልእክት እደመድማለሁ።

1. ሕዝባዊ ትግል ብዙ ውጣወረዶች ያሉበት ነው ነው። የጠላት ኃይል በስልጣን ላይ ለመቆየት በተለይ በሀገር ውስጥ የማይፈጥረው እንቅፋትናና የማይፈነቅለው ድንጋይ ስለማይኖር በርካታ ፈታኝ የሆኑ፤ ተስፋን ሊያደበዝዙ የሚቃጡ ሁኔታዎች ይገጥማሉ። ዋናውና ወሳኙ ጉዳይ ግን መታገል ብቻ ሳይሆን ችግሮችን ተቋቋሞ ትግሉን ዳር ለማድረስ በጽናት መታገል ነው። ሕዝባዊ ትግል ምን ጊዜም የኋላ ኋላ አሸናፊ መሆኑ ስለማይቀር ለትግል መሳካትና ግብ መድረስ ጽናት ዋናው መሣሪያ ነው።

2. ትግሉን ከማጠናከር አንጻር የትግሉ ታክቲክና ስትራቴጂ እንደየሁኔታው መለዋወጥ ያለበት ቢሆንም፤ አዳዲስ ሁኔታዎችን ከዘመኑ እድገቶች ጋር እያገናዘቡ መሄድ አስፈላጊ ቢሆንም አላማችንን ወይም ግባችንን ማለትም ፡ የሕዝብ መብት መረጋገጥን፤ ዴሞክራሲን ፤ ፍትህ ርትሕን፤ እኩልነትን፤ የሕግ የበላይነትን ፤ የሀገር ሉአላዊነትን ወዘተ.... ሊለውጡ በሚችሉ ወይም ጥያቄ ውስጥ ሊያስገቡ በሚችሉ የትግል ስትራቴጂና ታክቲክ መከተል የለብንም ።

3. በህብረተስቡ ውስጥ ያሉ ዜጎች አመለካከታቸው፤ አስተሳሰባቸው፤ ፍላጎታቸው፤ እምነታቸው ወዘተ... አንድ አይደለም ፤ አንድ ሊሆንም አይችልም። ስለሆነም የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች በሕብረተሰብ ውስጥ መፈጠራቸው ብዙ ሊያስደንቅ ወይም ሊያድደናግጥ የሚችል ክስተት

አይደለም። የተፈጥሮ ሕግ ነው። በዓላማው ላይ በግቡ ላይ ተመሳሳይ አቋምና እምነት እያላቸው ከዚያ መለስተኛ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሊለያዩ ይችላሉ። ዛሬ እናነተ በኢሕአፓ ወክንድ ሥር መደራጀታችሁ ተቃውሞ ሊያስከትል ሊሆን አይገባም። የመረጣችሁትን ለሀገርና ለወገን ይበጃል ብላችሁ ያመናችሁበትን ይዛችኋል። ሌላው በፈለገው ድርጅት መደራጀት መብቱ ነው። እንዲይያውም የተለያዩ ድርጅቶች መኖር ለዴሞክራሲ አስፈላጊ ነው። አላማቸውና ግባቸው አንድ የሆነ ማለትም በአገር ሉዓላዊነት፤ በሕዝብ መብት መረጋገጥ፤ በደሞክራሲ፤ በሕግ የበላይነት መስፈን ወዘተ.... የሚያምኑ ሃይሎች አምባገነን ኃይልን ታግሎ ለማስወገድ ህብረት መፍጠር አለባቸው። ድርጅታችን ኢሕአፓ በዚህ ላይ ጽኑ እምነት ሳለለው የኢሕአፓ ወክንድ እምነትም ይህ መሆን አለበት።

በርካታ የኢሕአፓ አባላት ታጋይ ይሞታል እንጅ ትግል አይሞትም የሚል መፈክር በማሰማታት ራሳቸውን ለቆሙበት አላማ አሳልፈው ሰጥተዋል። እነዚህ ሰማእታት ውድ ህይወታቸውን የሰጡት የሕዝብን መብት የሚያረጋግጥ ፤ ሥልጣንን ከሕዝብ የሚያመንጭ፤ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት፤ የሀገር ሉዐላዊነትን የሚያስጠብቅ ዴሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ ሥርዓትን በሀገራችን እውን ለማድረግ ነበር። ዛሬ እነዚህ ወጣቶች በኢሕአፓ ወክንድ ተሰባስበው ሰማታቱ ህይወታቸውን የሰጡበትን አላማ እውን ለማድረግ ትግሉን ለማካሄድ ቆርጠው መነሳታቸውን የስማእታቱ መፈክር ትክክለኛነቱን ከማረጋገጡም በላይ ለሕዝባችን አለኝታንና ተስፋ የሚሰጥ ነው።

ውጣ ውረዱ፤እንቅፋቱ ሊበዛ፤ ጊዜውም ሊረዝም፤ ቢችልም ሕዝባዊ ትግሉ ምን ጊዜም አሸናፊ መሆኑን አምነን ትግላችን እናጠናክር።

ትግላችን የተቃና ይሁን።

መልካም ስብሰባ መልካም በዓል ይሁንላችሁ

መስከረም 2004